ለዚህም ተግባር አጋዥ የሚሆኑ እንደ ኮምፒውተር፣ ላፕቶፕ ፣ ፕሪንተር ፣ ፋክስ ፣ ስካነርና ፎቶ ኮፒ የመሳሰሉ የቴክኖሎጅ መሣሪያዎች ተገዝተው ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች በማስራጨት ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህም ሌላ በዳታ ቤዝ ፣ ኔትወርኪንግ፣ ሶፍትዌር፣ መሠረታዊ ኮምፒውተር እውቀትና በኢንተርኔት አጠቃቀም ዙሪያ የሰው ሃይልን የማብቃት ሥራ በመሠራቱ በክልሉ በየእርከኑ የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት አመራሮች እና ሠራተኞች ሴት 3,500 ወንድ 8,000 በድምሩ 11500 ሠራተኞች በተለያዩ የቴክኖሎጅ ዕውቀት ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደ ተግባር ተሰማርተዋል፡፡

**በክልላችን የቴክኖሎጂ ልማትን ለማፋጠን በቁርጠኝነት እንሠራለን!**

**S/N/N/P/R/S/**
**Information Communication Technology Agency**

# ስመረጃ

- *ኤጀንሲ ሥራ አስኪያጅ ቢሮ*
  ☎ *04-62-20-65-72*
- *ኢኮቴ የሥራ ሂደት*
  ☎ *04-62-21-49-63*
  *ፋክስ 04-62-20-93-86*
  🖂 *1157*

**Website – www.snnprcapacity.gov.et**



**S/N/N/P/R/S/**
**Information Communication Technology Agency**

**በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት**
**የኢንፎርሚሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኤጅንሲ**
**South Nations Nationalities and People’s Regional State**
**Information Communication Technology Agency**




ዓለም ወደ አንድ መንደር/Globalization /

የካቲት 2002

በአቅም ግንባታ ሴክተር የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን የሥራ ሂደት በየወሩ የሚዘጋጅ

## የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ

## S/N/N/P/R/S INFORMATION COMMUNICATION TECHNOLOGY

### አጠቃላይ ገጽታ

የደቡብ/ብ/ብ ሕ/ክ/መ ኢኮቴ ኤጀንሲ ከ1995-1996 ዓ.ም ድረስ በአቅም ግንባታ ቢሮ በኤክስፐርት ደረጃ ከጥር 1996- 1998 ዓ/ም በቡድን ከጥር 1998-2000 ዓ፣ም ድረስ በመምሪያ ደረጃ ከነሃሴ 2000-ጥቅምት 2002 ደግሞ በስራ ሂደት ሲሰራ ቆይቶ በክልሉ፧ በተደረገው የሴክተር መስሪያ ቤቶች አዲስ አደረጃጀት ከጥቅምት 2002 ዓ.ም ጀምሮ ራሱን ችሎ በኤጀንሲ ደረጃ በአዋጅ ተቋቁሞ የተጣለበትን ሃላፊነትና ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛል።

### ራዕይ

የክልሉ ህብረተሰብ ሥራና ሕይወት በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖ ማየት፡

### ተልዕኮ

መረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂን በማልማት እና በሁሉም የክልሉ ተቋማትና ህብረተሰብ በስፋት በመጠቀም መረጃና መገናኛቴክኖሎጂለክልሉ እድገት የሚሰጠውን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ ማሳደግና የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻል ።

*S/N/N/P/R/S/G/C/P*

### እሴቶች

- *ለደንበኛ እርካታ ቅድሚያ ትኩረት መስጠት፣*
- *የዜጎችን ተሳትፎ ማጎልበት፣*
- *ለመልካም አስተዳደርና ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አጋርነትን ማረጋገጥ፣*
- *ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር መራመድ፣*
- *በቡድን የመሥራት መንፈስን ማስፈን፣*
- *የግልፅነት የተጠያቂነትንና የአሳታፊነትን መርሆን ማስፈን፣*
- *አዳዲስ እውቀቶችንና አሠራሮችን በመፈለግ ጥቅም ላይ ማዋል፣*

## በኤጀንሲው የሚሰጡ አገልግሎቶች

- የኔትወርክ ዝርጋታ ማካሄድ፣
- ሶፍትዌር ዴብሎፐመንት ፣
- አድቫንስና መሠረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና መስጠት ፣
- ጥገናና ሌሎች አገልግሎች ፣
- የቪዲዮ ኮንፍረንስንግና አግልግሎት
- ድፋፋዊ ክትትል ፣
- የማማከር አገልግሎት ፣
- ስታንዳርድ የማዘጋጀት ፣ የመስጠትና የመቆጣጠር፣
- የግሉን ሴክተር ICT መደገፍና ማልማት ፣
- የማህበረሰብ መረጃ ማዕከሎችን ማቋቋም ፣
- የሙያ ፈቃድና ማረጋገጫ መስጠት ፣

*S/N/N/P/R/S/G/C/P*

መንግሥት በማስፈጸም አቅም ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ ከሚተገብራቸው ፕሮግራሞች አንዱ የኢኮቴ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ሲሆን ይህም ለአዲሱ ኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባታ ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈንና ፈጣን አገልግሎት አሰጣጥ ፣ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ የተፋጠነ እንዲሆን ፣ በትምህርት፣ በጤናና በግብርናው መስክ የኢኮኖሚን ልማት ፈጣን ለማድረግ፣የተቀናጀ የበጀት አሰራርን /IBEX/ በመዘርጋት የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ፣ ከቀበሌ እንስቶ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ መረጃዎችን በቀላሉ መለዋወጥ የሚቻልበትን አሰራር ለመዘርጋት እንዲያስችል የተነደፈ ፕሮግራም ነው ።

የክልሉ ኢኮቴ ኤጀንሲ ህብረተሰቡን ማዕከል ያደረገ የመረጃ ማዕከላት በማደራጀት ፣ በክልላችን እስከ ገጠር ወረዳ ድረስ የተዘዋዋሪ ችሎት አገልግሎት በመስጠት ውጣ ውረዶችን ያስቀረ አሰራር የፈጠረ ሲሆን በቪዲዮ ኮንፍረንስ ሀሳብ መለዋወጥና ወቅታዊ መረጃዎችን ማግኘት አስችሏል ።

ከዚህም በላይ በክልሉ ባሉ ሴክተር ቢሮዎች እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ በመውረድ ኋላቀር አሰራሮችን በዘመናዊ ቴክኖሎጅ በመቀየር በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል ። ሥራዎችን ከማቀላጠፍ አንጻር የኔትወርኪንግ ፣ ዳታቤዝ ፣ ኢንተርኔት አገልግሎቶችን በማስፋፋት መረጃዎችን በቀላሉ ማስተላለፍና መቀበል አስችሏል ።

*S/N/N/P/R/S/G/C/P*